# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

***ታህሳስ 13 ቀን 2005 ዓ.ም***

**በትግራይ ክልል በአዲግራት ከተማ ግጭት ተቀሰቀሰ፤**

**ወያኔ አጣብቂኝ ውስጥ በመግባቱ የሙስሊሙን ጥያቄ ለማዳፈን ሲል የፈበረከው የፈጠራ ክስ ይቀጥል ተባለ፤**

**ሙስሊም የሆኑ ከሚኒስትር እስከ ወረዳ አስተዳዳሪ ድረስ ያሉ ባለስልጣናትም ሊታፈሱ ነው ተባለ፤**

**መኮንኖች ተይዘው ጦር ኃይሎች መኮንኖች ክበብ አጠገብ በሚገኝ እስር ቤት እየታጎሩ መሆኑ ተጋለጠ፤**

የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ሙስሊሙ ማህበረሰብ ያነሳውን ጥያቄ ለማዳፈን ሲሉ በተለያዩ ከተሞች በፌዴራል ፖሊስ እና በተወርዋሪ ፖሊሶች ከባድ ጉዳት እያደረሱ ሲሆን በተመሳሳይ ሰሞኑን በትግራይ ክልል በአዲግራት ከተማ ነዋሪ ከሆኑ የሙስሊም አማኞች ጋር ግጭት ፈጥረው በፌዴራል ፖሊስ እና በክልሉ ልዩ ኃይሎች በተወሰደ እርምጃ ብዙ ሰዎች ለጉዳት እንደተዳረጉ ከስፍራ የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

የአዲግራት ሙስሊሞች የሚቀበሩበት መቃብር ቦታ ህዝበ ሙስሊሙን ሳያወያዩት እና ሳያነጋግሩት በግዴለሽነት እና በመናቅ በግሬደር ለማፍረስ ሙከራ በማድረጋቸው በተነሳ ተቃውሞ ብዙ ጉዳቶች እንደደረሰ ከስፍራው ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

ቁርዓን በማይፈቅደው መልኩ የአዲግራት ከተማ መስጊድን በፌዴራል ፖሊስ እና በልዩ ኃይል ከብበው ወደ ውጭ እንዳይወጡ በማድረግ አግተው ሲያሰቃዩዋቸው ከመቆየታቸውም በላይ የመቃብር ቦታውን ለማፍረስ ሙከራ ሲያደርጉ ያሰሙትን ተቃውሞ በካሜራ በመቅረጽ ህዝበ ሙስለሙን ሲያስፈራሩ እንደነበረም ተጋልጦዋል፡፡

ከረዥም ዘመናት ግዜ ጀምሮ ሕዝበ ሙስሊሙ ሲጠቀምበት የነበረውን የሙስሊሙ መቃብር ሕዝቡን ሳያወያዩና ሳያነጋግሩ ድንገት ማፍረስ በመጀመራቸው በተቀሰቀሰ የህዝበ ሙስሊሙ ቁጣ በአዲግራት ከተማ ከባድ ጉዳት መከሰቱ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

በአዲስ አበባ በአወሊያና በአንዋር መስጊድ ከተከሰተው ተቃውሞ ጋር የሙስሊሙ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባሎች ናቸው የተባሉትን አፍስው ለእስር የዳረጉዋቸው ከመሆኑም በላይ ዋነኛው ተጠሪ የሆነውን አቡበከር የተሰኘውን የአፋር ብሔር ተወላጅ ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ እንዲፈታ የአፋር ብሔር ሽማግሌዎች አዲስ አበባ መጥተው እንደነበረም የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አስረድቶዋል::

በአሁኑ ሰዓት በቃሊቲ እስር ቤት ታጉረው የሚገኙት የሙስሊሙ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አመራሮች የክስ ሂደታቸው ቀጥሎ ታህሳስ 8 ቀን 2005 ዓ.ም ፍርድ ቤት ተገኝተው ዓቃቤ ህግ ያቀረበውን የሀሰት ክስ መቃወሚያ ያቀረቡ ቢሆንም የወያኔ ሹመኛ ዳኞች ውድቅ አድርገው ክሱ እንዲቀጥል መወሰኑ ታወቀ::

ሰኞ ዕለት ታህሳስ 8 ቀን 2005 ዓ.ም በከፍተኛ ፍርድ ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት ከጠዋቱ 3 ሰዓት ተኩል የቀረቡት የመስሊሙ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባሎች ክሱ ህገ መንግስቱን የጣሰና ህገወጥ በመሆኑ ክርክር ሳያስፈልገን ተዘግቶ በነጻ ያሰናብተን ብለው ለፍርድ ቤቱ አቅርበው የነበረው ሀሳብ ሙሉ ለሙሉ ውድቅ ተደርጎ ክሱ ተገቢና ትክክለኛ በመሆኑ ሂደቱ ይቀጥል ሲል ውሳኔ ማሳለፉ ታውቆዋል::

ባለፈው ሳምንት ህዳር 27 ቀን 2005 ዓ.ም በሌሉበት ለሰኞ ታህሳስ 8 ቀን ተቀጥረው የነበሩት የሙስሊሙ መፍትሄ አፈላላጊ አመራሮች ከወትሮው በተለየ ሁኔታ እጃቸው በካቴና ታስሮ ፍርድ ቤት የቀረቡ ሲሆን ልደታና አካባቢዋ በደህንነት..... በፌዴራል ፖሊሶች እና በአዲስ አበባ ፖሊሶች ተወጥራ የዋለች ሲሆን ከኮካ ማዞሪያ እስከ ሜክሲኮ....ከአብነት እስከ ልደታ ጥብቅ ጥበቃ ሲደረግ እንደዋለም ለማየት ተችሎዋል:: 6 የፌዴራል ፓትሮሎች በፍርድ ቤት ዙሪያ በተጠንቀቅ ቆመው እንደነበር የተስተዋለ ሲሆን እያንዳንዱ ፓትሮል 6 ፖሊሶችን ጭነው እንደነበረም ለማረጋገጥ ተችሎዋል::

በዕለቱ በዋለው ችሎት ህገ መንግስቱን በአመጽ ለመናድ አስረዋል የሚለውን ክስ አቃቤ ህግ በጽሁፍ እና በቃል ያቀረበ ቢሆንም እስረኞቹ ግን እኛ የታሰርነው ዜጎች ንጹህ ኢትዮጵያውያን ነን ...አሸባሪ አይደለንም .....አሸባሪው የወያኔ ቡድን ነው .....ወንጀል የተፈጸመብን ሕግ አክባሪ ዜጎች ነን......ህገ መንግስቱን እየናደ ያለው እራሱ ወያኔ ነው ብለው መልስ በመስጠታቸው የተበሳጩት የወያኔ ካድሬ ዳኞች ተከሳሾቹን በመገላመጥ እና በማስፈራራት ያቀረቡትን ሀሳብ ሙሉ ለሙሉ ውድቅ አድርገው ለጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥተዋል::

በቅርቡ ተሹመው ስራ የጀመሩት የወያኔ ካድሬ ዳኞች ባስተላለፉት ትዕዛዝ መሰረት እስረኞቹ ህገ መንግስቱን ለመናድ የተንቀሳቀሱ መሆናቸውን በመግለጽ ክሱ ሊቀጥል ይገባል ሲሉም መወሰናቸው ታውቆዋል::

በዚህም መሰረት ዓቃቤ ህግ አሉኝ ያላቸውን የሰው ምስክሮች ከጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ለተከታታይ 10 ቀናት እንዲያቀርብ ሲሉም ቀጠሮ መስጠታቸው ታውቆዋል፡፡

እስረኞቹ በጠበቆቻቸው አማካኝነት ዓቃቤ ህግ ያቀረበውን ክስ ከህገ መንግስቱ ጋር እያጣቀሱ መቃወሚያ ያቀረቡ ቢሆንም ካድሬ ዳኞቹ ግን ሳይቀበሉት የዓቃቤ ህጉን ሀሳብ ብቻ ተቀብለው የክስ ሂደቱ እንዲቀጥል ሲሉ ውሳኔ በማስተላለፋቸው ጉዳዩን የሚከታተሉ የህግ ባለሙያዎች በእጅጉ ማዘናቸውን ሲገለጹ ተደምጠዋል፡፡

ሽብርተኛ ናቸው.....ከሽብርተኞች ጋር ግንኙነት አላቸው ተብሎ የቀረበባቸውን ክስ ያስተባበሉት እስረኞቹ በአሁኑ ሰዓት ወያኔ አጣብቂኝ ውስጥ በመግባቱ እና የሙስሊሙን ጥያቄ ለማዳፈን ሲል የፈበረከው የፈጠራ ክስ እንጂ እኛን አይመለከተንም ያሉት እስረኞቹ እውነት እና ንጋት እያደር የሚጠራ በመሆኑ አንዳችም ፍርሀት አይሰማንም ሲሉ በችሎቱ በጩኸት ማስደመጣቸውንም ሂደቱን የተከታተሉ ወገኖች ገልፀዋል፡፡

የወያኔው ከፍተኛ ባለስልጣን የነበረውና በቅርቡ ከኦህዴድ ስራ አስፈጻሚነት እና ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትርነት የተነሳው ጁኔዲ ሳዶ ባለቤት ያቀረበችው ክሱ በተናጠል ይታይልኝ ጥያቄ ውድቅ ተደርጎ ከሌሎቹ 28 ተከሳሾች ጋር አብሮ እንዲታይ ብሎም ውሳኔ መሰጠቱ ታውቆዋል፡፡

ባለቤቲ የቤት እመቤት እና ምንም የማታውቅ ንጹህ ኢትዮጵያዊ ነች በማለት የኢትዮጵያን ህዝብ ሲማጸንና የወያኔን ቡድን ደግሞ የሚያጋልጥ ጽሁፍ በተለያዩ ጋዜጦች ላይ በማውጣቱ የተበሳጩት የወያኔ ባለስልጣናት በተለይ የህወሀቱ የፌዴራል ፖሊስ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው አበበ ዘሚካኤል እስከ አሁን ዝም ያልነው ይበቃል ከእንግዲህ እርምጃ እንወስዳለን ብሎ ያስፈራራው መሆኑን ያስታወሱት ጉዳዩን የሚከታተሉ ወገኖች ጁኔዲ ሳዶ በደህንነቶች በሚደርስበት ወከባና እንግልት በመደናገጥ ለህክምና ብሎ ወደ ውጭ ሀገር የወጣ ሲሆን ሚስቱ ግን በቃሊቲ እስር ቤት ሆና የክስ ሂደትዋን እየተከታተለች መሆኑም ታውቆዋል፡፡

የህዝበ ሙስሊሙ ተቃውሞ ከግዜ ወደ ግዜ እየሰፋና እያደገ በመምጣቱ በወያኔ ቡድን ባለስልጣናት መሀል ጭምር ክፍፍል የፈጠረና ከፍተኛ ፍርሀት ውስጥ የጣላቸው በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት የሙስሊሙ ጉዳይ ለወያኔ የስጋት ቀጣናው መሆኑንም የራሳቸው ካድሬዎች በመናገር ላይ ይገኛሉ፡፡

በቅርቡ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ከተሾሙት ሶስት ባለስልጣናት መሀከል አንዱ የሆነው የኦህዴዱ ምክትል ሊቀመንበር ሙክታር ከድር ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዳለው በመታወቁ ለቁጥጥር እንዲያመች ስልጣን ተሰጥቶት የቅርብ ክትትል እያደረጉበት መሆኑን የጠቆሙት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ሌሎች ሙስሊም የሆኑ ከሚኒስትር እስከ ወረዳ አስተዳዳሪ ድረስ ያሉ ባለስልጣናትንም_በአይነ ቁራኛ እየተከታተሉዋቸው መሆኑን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በሌላ ዜና በአንድ ወገን የበላይነት የታጠረው የወያኔ መከላከያ ሚኒስትር በቅርቡ በህገ ወጥ መንገድ በተሾሙት ጄኔራል መኮንኖች መልሶ ህወሀት የበላይነቱን እያጠናከረ በመሆኑ በመኮንኖቹ

መሐከል ክፍፍሉ እያፈጠጠና ገሀድ እየወጣ በመምጣቱ ስውር እስራት መጀመሩን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ፡፡

በተለያዩ የጦር ክፍሎች ውስጥ የሚሰሩ ወጣት መኮንኖች በመከላከያ ውስጥ በሚሰራው አድሎአዊ አሰራር ምክንያት ጥያቄ እያነሱ በመምጣታቸው ከተለያዩ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር እያያዙ ለእስራት እና ለአፈና እየተዳረጉ መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

በ1997 ዓ.ም በተደረገው የሀገር አቀፍ ምርጫ የወያኔ ቡድን መሸነፉን ያመኑት የህወሀት ጄኔራሎች በስራቸው የነበሩትን  የኦሮሞና የአማራ ብሔር ተወላጅ ከፍተኛ መኮንኖች ቅንጅትን ደግፋችሁዋል በሚል ከስራ ያባረሩዋቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ለእስር የዳረጉዋቸው መሆኑን ያስታወሱት ምንጮቹ አሁንም በተመሳሳይ በመከላከያ ውስጥ በሚደረገው አድልኦ በመበሳጨት የመብት ጥያቄ የሚያነሱ መኮንኖችን እያፈኑ ደብዛቸውን እያጠፉዋቸው  እንደሆነ ምንጮቹ ጠቁመዋል፡፡ ሰሞኑን ከምዕራብ እዝ እና ከአዲስ አበባ ከሚገኙ ልዩ ልዩ ክፍሎች ቁጥራቸው የበዛ መኮንኖች ተይዘው ጦር ኃይሎች መኮንኖች ክበብ አጠገብ በሚገኝ እስር ቤት የታጎሩ መሆኑን ያጋለጡት ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ በተለይ የኦሮሞ እና የአማራ ብሔር ተወላጆች እንደሚበዙም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በአዲስ አበባና በደብረዘይት በሚገኙ የመከላከያ ኢንጅነሪንግ ስር ባሉ መስሪያ ቤት የተለያዩ ምህንድስና ሙያ ያላቸው መኮንኖች ላይ ከፍተኛ የእስራት ዘመቻ እየተደረገባቸው እንደሚገኝ የጠቆሙት ምንጮቹ  ከአምቦ ጋፋት ኢንጅነሪንግ (የጦር መሳሪያ ማምረቻ..... ከደብረዘይት የመኪና መገጣጠሚያ.....ከአየር ኃይል መኮንኖች ጭምር እየታፈሱ ለእስር እየተዳረጉ መሆኑን የምንጮቹ ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

በመከላከያ ውስጥ ቀድሞ የነበረው ልዩነት በተለይ ማን እንደሾማቸው ባልታወቀ ሁኔታ በቅርቡ 34 ጄኔራሎች ማዕረግ ከተሰጣቸው በሁዋላ በተፈጠር የውስጥ ጉምጉምታ የተደናገጡት የህወሀት መኮንኖች በምህንድስና ሙያ የተማሩ መኮንኖች ላይ ባነጣጠረ መልኩ የጀመሩትን እስራት እና መሰወር አስፋፍተው የቀጠሉበት በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት በመከላከያ ውስጥ ትርምስ ተፈጥሮ እንደሚገኝ የምንጮቹ ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

የአንድ ወገን የበላይነት ይወገድ..... ተቁዋሙ ብሔራዊ እንጂ ክልላዊ አይደለም..... ሁሉም ለሀገር እንጂ ለግል የሚል አቁዋም ያስወግድ...... በማለት ወጣት መኮንኖቹ በሚያነሱት ጥያቄ የተደናገጡት የህወሀት ጄኔራል መኮንኖች በመከላከያ ስር በተዋቀረው ወታደራዊ ደህንነት ሰራተኞች አማካኝነት ውስጥ ውስጡን እየለቀሙ ገሚሱን ለእስር ሱዳርጉዋቸው ገሚሶቹን ደግሞ የት እንደሚያደርሱዋቸው እንዳልታወቀም ከምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በመከላከያ ውስጥ በተፈጠረ ዝርክርክ አሰራር የተነሳ የሀገር እና የህዝብ ሀብት እየባከነ ከመሆኑም ባሻገር የህወሀት ጄኔራል መኮንኖች በተለያዩ መንገዶች እየዘረፉ እና በዘመዶቻቸው ስም እያሸሹ መሆኑንም ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

ጄኔራል መኮንኖቹ የኢትዮጵያ ህዝብ ሀብት የሆኑትን የተለያዩ ሚኒስትር መስሪያ ቤት በብልሽት የቆሙ መኪኖችን እየሰበሰቡ በኪሎ እንዲሸጡ በማድረግ በሚስቶቻቸው እና በዘመዶቻቸው ስም ከፍተኛ ገንዘብ እያግበሰበሱ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

እንደ ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ከሆነ በሀገሪቱ ውስጥ ተበላሽተው የቆሙ ከባድ .....ቀላልና መሀከለኛ መኪኖች ከያሉበት ተለቅመው እንዲወሰዱና ዱከም ለሚገኘው ለመከላከያ ኢንጅነሪንግ ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ በኪሎ እንዲሸጡ በማድረግ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር እያግበሰበሱ ከመሆኑም ባሻገር እራሳቸው ለሚጠቀሙበት እቃ የማስጫኛ ትራንስፖርት ሂሳብም ከመንግስት ካዝና ወጪ መደረጉንም ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

የመከላከያ ኢንጅነሪንግ ስር ካሉ ፋብሪካዎችም እቃ በዱቤ እያወጡ አንዲሸጡ በማድረግ የመኮንኖቹ ሚስቶች አንቱ የተባሉ ቱጃር ለመሆን የበቁ መሆኑን ያጋለጡት ምንጮቹ እርስ በርስም ክፍፍሉ ላይ ከፍተኛ ሽኩቻ ውስጥ መግባታቸውን ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

በዚህ ድርጊት እየተሳተፉ የሚገኙት በሙሉ የህወሀት ጄኔራል ሚስቶች ብቻ መሆናቸውን ያጋለጡት ምንጮቹ ደርግን ለመጣል መስዋዕት የከፈልነው እኛ ህወሀቶች ብቻ ነን እያሉ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይም እየተዛበቱበት መሆኑን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በተለያዩ ሰበቦች በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ከመንግስት ካዝና ወጪ እየተደረገላቸው ከመሆኑም ባሻገር ልጆቻቸውን በኢትዮጵያ ህዝብ ሀብት ውጭ ሀገር ልከው እያስተማሩ መሆኑንም ምንጮቹ ጨምረው አስረድተዋል፡፡

በተለይ ጥቂት የአድዋ ተወላጅ ጄኔራል መኮንኖች በዘመዶቻቸው በኩል የወርቅ ንግድ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በአሁኑ ሰዓት በሀገር ውስጥ ስራ ቀዝቅዞ በከፋ ችግር ውስጥ የሚገኙ የኮንስትራክሽን ባለሙያዎችን እያባረሩ ጨረታውን ሁሉ ለራሳቸው ብቻ እየወሰዱ መሆኑን ገልፀዋል፡